

# 14

# መነፍሳዊ ጡንቻ

## 14-1

በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሰዎች የተለያየ ጠቃሚ ምግብን በመመገብ እንዲሁም የተለያየ እንቅስቃሴና ልምምድ በማድረግ ደካማ የነበረውን አካላቸውን ሲያዳብሩ ይታያሉ። ሥጋችን ጥሩ አቋም ላይ እንዲሆን ልዩ ልዩ ጥረት እንደምናደርገው ሁሉ፥ መነፈሳዊ ሕይወታችንም እንዲጠነክር የማያቋርጥ ልምምድ ማድረግ ይገባናል። ክርስቲያን መነፈሳዊ ሕይወቱ ሲያድግና ሲበረታ፥ የተለያየ ከባድ የኑሮ ሸክም መሸከምና ማለፍ ይችላል። ሥጋን ማዳበር ብዙ ጊዜ በወጣቶች ሕይወት የሚታይ ሲሆን፥ መንፈሳዊ አካልን ማዳበር ግን ለወጣት ብቻ ሳይሆን ሽማግሌዎችንም ይጨምራል። መንፈሳዊ ጡንቻን ስለማዳበር የሚገልጹ ጽሁፎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያየ ሥፍራዎች ተጠቅሰው እናነባለን። በቅድሚያ ግን 1ኛ ዮሐንስ 2፥12-14 ያለውን እንመልከት። ዮሐንስ እዚህ ላይ ሦስት ክፍሎችን ይገልጻል። ይኸውም፥ 1ኛው፥ ልጆች፣ 2ኛው፥ ጎበዞች፣ 3ኛው፥ ደግሞ አባቶች ይላቸዋል። እነዚህ ዮሐንስ የገለጻቸው 3 ክፍሎች በሥጋዊ ዕድሜ እንዳልሆነ ግልጽ ነው።

## ልጆች

“ልጆች ሆይ ኃጢአታችሁ ስለ ስሙ ተሰርዮላችኋልና እጽፍላችኋለሁ” ይላል። የታወቀው ኒቆዲሞስ በሞራሉ ጠንቃቃና በሃይማኖቱ ብቁ የሆነ ሰው ቢሆንም፥ ኢየሱስ ግን “ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስ የተወለደ ግን መንፈስ ነው” በማለት እንደገና መወለድ እንደሚያስፈልገው ነገረው (ዮሐ. 3፥6)።

ሙሴ የእሥራኤልን ሕዝብ ለብዙ ዘመን ለብቻው ይመራ ነበር። ዕድሜው እየገፋ በሄደበትም ዘመን ሌላ የውጭ እርዳታ የፈለገበት ጊዜ አልነበረም። ሙሴ ከሞተ በኋላ ግን እግዚአብሔር ኢያሱን ጠራው። ኢያሱ ለአርባ አመት ሙሉ ሙሴን በመታዘዘና በፍጹም ታማኝነት የሚሰጠውን ትእዛዝ ሁሉ በመቀበል በቅንነት አገልግሎታል። ሙሴ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር መሪነቱን እንዲወስድ ጠራው። ኢያሱም የመሪነቱን ስፍራ ሲይዝ፥ ታላላቅ ውሳኔዎችን መወሰን ብቻ ሳይሆን፥ የተለያየ ተቃውሞም መጋፈጥ እንዳለበት ተረዳ። በዚህ ጊዜ ያየው የራሱን ድካም ስለነበር ልዩ ፍርሃት ልቡን ሞላው። እግዚአብሔርም የኢያሱን ሁኔታ ተመልክቶ ወደፊት የሚሰጠውን ድል አረጋገጠለት። የኢያሱን መደናገጥ አይቶ እግዚአብሔር በመደጋገም በተስፋ ቃሉ ያጽናናው ነበር። “ለሙሴ እንደነገርኩት የእግራችሁ ጫማ የሚረግጠው ቦታ ሁሉ ለእናንተ ሰጥቻለሁ፤ ከሙሴ ጋር እንደነበርኩ ሁሉ ከአንተም ጋር እሆናለሁ” እያለ ኢያሱን ሲያጽናናው እንሰማለን። ይህ ብቻ ሳይሆን በጠላቶቹ ላይ ደግሞ ድልን እንደሚሰጠው አረጋግሎለት ነበር።

እግዚአብሔር ለኢያሱ መንገዱ ሁሉ ቀላል ይሆንልሃል፥ ፈተና አያጋጥምህም የእሥራኤልም ሕዝብ አይነሳብህም ብሎ ተስፋ አልገባለትም። ችግሩን በመገንዘብ የሚያጋጥመውን ፈተናና ጥላቻ

በመመልከት ያንን የሚቃወምበትን ኃይል ግን እንደሚሰጠው አረጋገጠለት። ኢያሱም እግዚአብሔር የገባለትን ተስፋ በመጠበቅ ወደ ፊት ገፋ፤ ድልንም አገኘ። ኢያሱ ኃላፊነቱን ከተቀበለ በኋላ መጀመሪያ ያጋጠመው ጦር ሜዳ ኢያሪኮ ነበር። በዚያም የነበረውን አስቸጋሪ ሁኔታ በመገንዘብ በተደናገጠበት ወቅት ዓይኑን አነሳ። "እንዲህም ሆነ፤ ኢያሱ በኢያሪኮ አጠገብ ሳለ አይኑን አንስቶ ተመለከተ። እነሆም የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ የያዘ ሰው በፊቱ ቆሞ ነበር። ኢያሱም ወደ እርሱ ቀርቦ ከእኛ ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህን? አለው። እርሱም እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቻለሁ" አለ። ኢያሱ ይህ ከእግዚአብሔር የተላከ መልእክተኛ መሆኑን ባወቀ ጊዜ ያደርገው ነገር ቢኖር ወድያው በግንባሩ ተደፍቶ መስገድ ነበር። መስገድ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ሊናገረው የሚፈልገው ነገር ለማወቅ በመጓጓት "ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድነው?" በማለት ጠየቀ። ያም መልዕክተኛ እግዚአ ብሔር የነገረውን ትእዛዝ ወይም ሃሳብ ሲገልጽለት እንደዚህ አለው። "አንተ የቆምክበት ሥፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ" አለው። ኢያሱም እንደዚሁ አደረገ። በዚህም እግዚአብሔር በዚያ ሥፍራ እንደነበረ አወቀ። መልዕክተኛው ለኢያሱ የድል ሚስጥር ምን እንደሆነ ሲገልጽለት፥ "የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግም ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቃናልሃል፤ ይከናወንልሃልም" አለው (ኢያሱ 1፥8)። እንግዲህ መንፈ ሳዊ ጡንቻ ለማውጣት ከፍተኛ ሚስጢሩ እራስን በእግዚአብሔር ቃል መሙላት ነው። ዳዊት በመዝ ሙር እንዲህ ይላል "ቃልህን በልቤ እሸሽጋለሁ በአንተ ላይ ኃጢአትን እንዳትሰራ" (መዝ. 119፥11)።

የእግዚአብሔርን ቃል በልባችን ማጠራቀም በየእለቱ ለሚኖረን መንፈሳዊ እርምጃ ስንቅና ትጥቅ ይሆንልናል። የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ በልባችን መያዙ ድልን ይሰጠናል ማለት አይደለም። ነገር ግን ቃሉን ሰምተን እንደ ቃሉ የታዘዝን እንደሆነ ነው። በልባችን ያጠራቀምነው የእግዚአብሔር ቃል እንደአስፈላጊነቱ ይናገረናል። ኃጢአት በምንሰራበት ወቅት ሁሉ ይገስጸናል፤ እንዴትም ደግሞ መመላለስ እንደሚገባን ያሳየናል። እንግዲህ በውስጣችን የእግዚአብሔር ቃል ሥራውን መስራት ሲጀምር ለእግዚአብሔር መታዘዝ እንጀምራለን። የሥጋና የመንፈስ እድገት የሚመሳሰሉበት ሁኔታ አላቸው። ይኸውም ማንኛውም ሰው በሥጋ ሕጻን ሆኖ እንደሚወለደው ሁሉ፥ እንዲሁም አንድ ሰው በመንፈስ እንደገና ሲወለድ እንደ ሕጻን መሆን እንደሚያስፈልገው ቃሉ ይናገራል። "እውነት እውነት እላችኋለሁ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕጻናትም ካልሆናችሁ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም" ይላል (ማቴ. 18፥3)።

ጤናማ ልጅ በሥጋው አስፈላጊውን ምግብ ካገኘ እድገት ያሳያል። መቀመጥ፣ መዳህ፣ መራመድ፣ በኋላም መሮጥ ይጀምራል። እያደረ አካባቢውን ማወቅና መለየት ከዚያም መናገርን ይለማመዳል። ዕድሜው እየጨመረ ሲሄድ ድግሞ ተማሪ ቤት ገብቶ የተለያየ ነገር ማወቅና መማር ይችላል። ጤናማ ልጅ በየጊዜው ከተለያየ የእድገት ደረጃ ይደርሳል ይኸውም ከሕጻንነት ወደ ልጅነት፣ ከልጅነት ወደ ጎልማሳነት ከዚያ ደግሞ ወደ ሙሉ ሰውነት ደረጃ ይደርሳል። አንዳንድ ሕጻን የሚገባውን እድገት የማያሳይበት ጊዜ አለ። የሚያሳዝነው ሥጋዊ አካሉ ትልቅ ይሆንና አንጎሉ ግን የትንሽ ልጅ አንጎል ይሆናል። በእድሜው ትልቅ ሆኖ የአንጎሉ እድገት ምናልባት የአራት አመት ልጅ አንጎል ይሆናል። ይኼ ጤናማ አይደለም። እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲፈጠር ያ ሰው ልዩ ዓይነት ጥንቃቄ እንዲደረግለት ያስፈልጋል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ በዓለም ውስጥ ያለውን ትግል መታገል ስለማይችል ልዩ ዓይነት እንክብካቤ ያስፈልገዋል (ዕብ. 5፥12-13)። አንዳንድ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ገና ሕጻናትና ያላደጉ በመሆናቸው ወተት እንደሚያስፈልጋቸው ሐዋርያው ጳውሎስ ይገልጻል (1ኛ. ቆሮ. 3፥1-3)። አንዳንድ ክርስቲያኖች ከዳኑ ብዙ ዘመን የሆናቸው ቢሆንም በጠባያቸው ግን አሁንም ሕጻናቶች ስለሆኑ እምነት አይጣልባቸውም። ኃላፊነት መቀበልና ውሳኔ መወሰንም አይችሉም። የዕድሜያቸው ሁኔታ በማየት እንዲሁም በኅብረተሰብ መካከል ያላቸውን አቋም በማየት ብዙ ሰዎች ከእነርሱ ትልቅ ነገርን ይጠብቃሉ። እድገት ያላቸው ክርስቲያኖች ናቸው ብለውም ይገምታሉ። ይሁን

እንጂ አይደሉም። ብዙ መጋቢዎች እንደ እነዚህ ዓይነቶቹን ለማሳደግ ብዙ ጊዜ ይፈጅባቸዋል። ያላደጉም ስለሆነ በጥንቃቄ መያዝ ያስፈልጋቸዋል። ልክ እንደ ሕጻናት በቀላሉ ሆድ ይብሳቸዋል፣ ይበሳጫሉ፣ “ይኼና ያ አልተደረገልኝም” ይላሉ። የራሳቸውን ፈቃድ ብቻ ያስቀድማሉ፤ ኃላፊነት ሲሰጣቸው ኃላፊነት አይቀበሉም። ቤተክርስትያን ምን እንደሚያደርግላቸው እንጂ እነርሱ ለቤተክርስ ትያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም። እንደገና ተወልደዋል፤ ግን አሁንም ሕጻናት ናቸው።

በ1ኛው ዮሐንስ ምዕራፍ 2 እንደተጻፈው፥ ልጆች ሁለት ነገር ያውቃሉ። አንደኛው ኃጢአታቸው እንደተሠረየላቸው ያውቃሉ። “ልጆች ሆይ ኃጢአታችሁ ስለስሙ ተሰርዮላችሁዋልና እጽፍላችኋለሁ” ይላል። ሁለተኛ ደግሞ፥ አብን ያውቃሉ። “ልጆች ሆይ አብን አውቃችኋልና እጽፍላችኋለሁ”። እነዚህ ሁለት ነገሮች ማወቃቸው ትልቅ ነገር ቢሆንም፥ እውቀታቸው በዚሁ ላይ ብቻ የተወሰነ ከሆነ ግን አሳሳቢ ይሆናል። እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚያስታጥቃቸው ሌላ እውቀቶች እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ብዙ ክርስቲያኖች ጌታን ወደ ማወቅ ደረጃ ይደርሳሉ። የኃጢአትንም ይቅርታ ይቀበላሉ፤ እግዚአብሔ ርም እንደሚወዳቸው ያውቃሉ። የሚያሳዝነው ግን እውቀታቸውና ልምምዳቸው ብዙ ጊዜ እዚህ ላይ ያቆማሉ። በቂ የሆነ የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ስለሌላቸው፥ መንፈሳዊ ሕይወታቸው ደካማና ልፍስፍስ ይሆናል። ልክ እንደ ህጻን ልጅ አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ታግለው ማሸነፍና እንዲሁም በራሳቸው መቆም አይችሉም። እንደእነዚህ ዓይነት ክርስቲያኖች ለጓደኞቻቸው ወይም ለቀረባቸው ሁሉ ምቹ ያልሆኑ፣ ለሚያሳድጋቸው መንፈሳዊ መጋቢ ደግሞ የሚያስቸግሩ ይሆናሉ። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በቤተክርስትያን ውስጥ ኃላፊነት እንዲይዙ መፍቀድ ችግርን መጥራት ይሆናል።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። እሜን!**